# በትምህርት ተቋማት የአምልኮ ሥርዓትን በሚመለከት የትምህርት ሚኒስቴር በህዳር 2000 ያወጣውን መመሪያ በሚመለከት ከበድር አለም አቀፍ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ፌደሬሽን እና አጋር ማህበራት የተሰጠ የአቋም መግለጫ

አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ ዘግናኝ እና የማይረሱ የጭቆና እና የስቃይ ዘመናትን አስተናግዳለች። ከራሳቸው የግል ጥቅም አለፍ ብለው የህዝብና የአገር እድገት እንደዚሁም ብልጽግና የማይገዳቸው መሪዎች አገሪቱን በቀላሉ ማንሰራራት ከማትችልበት የፓለቲካ፣ የታሪክ፣ የማህበራዊ ህይዎትና የኢኮኖሚ አሮንቃ ውስጥ ዘፍቀዋት አልፈዋል። ያራምዱት የነበረው ፓሊሲም ፍቅርን መተሳሰብን የጋራ ደህንነትን እና ጥቅምን መሰረት ያደረገ ሳይሆን በጥላቻ እና ከፋፍለህ ግዛው በሚል መርህ-ግብር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በህዝቦች መካከል መተሳሰብን ሳይሆን መከፋፈልን፣ መተማመንን ሳይሆን እርስ በርስ መጠራጠርን አስፍኖ አልፏል።

ለአንድ አገር እድገት መሰረት እንደዚሁም የለውጥ ራዕይ መፍለቂያ የሆነውን የትምህርት ተቋማትን ስናይም ትምህርት ከአድሎ የፀዳ አልነበረም። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚጋራው ጭቆና እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ከገዥው ክፍል እምነት የተለየ ሃይማኖት በመከተላቸው ከትምህርት እና መሰል የህዝብ አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆን ይቅርና ጥያቄውንም ማቅረብ አይችሉም ነበር።

ለአንድ እምነት የበላይነት እና የበላይ ጠባቂም ሆኖ የቆየው የነገስታት ዘመን በ1966 ካከተመ በኋላ እምነት የለሽ የሆነ አገዛዝ ለ17 አመታት ያክል በአገሪቱ ሰፍኖ ቆይቷል። ይህ ስርዓት ለሁሉም እምነቶች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ አቋም የነበረው ቢመስልም ለዘመናት ተጨቁነው እና ሙሉ መብታቸውን ተክደው የነበሩ ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ላይ የነበረው ጭቆና ግን እስከ ስርዓቱ መገባደጃ ድረስ ቀጥሎ ዘልቋል።

ጭቆና፣ አድሎና ስቃይ የወለደው የህዝቦች ትግል የኢትዮጵያዊያንን የእምነት ነጻነት እና እኩልነት በማያሻማ መልኩ ያረጋገጠ ህገ-መንግስትን እዉን በማድረግ የህዝቦችን የወል ድል በ1983 አረጋገጠ። ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችም እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የዚህ መብት ተጠቃሚ ለመሆንም በቁ። በተለይም ትምህርት ከሃይማኖታዊ አድሏዊነት የፀዳ መሆን አለበት በሚል ፓሊሲ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሙስሊሞችም ለመጀመሪያ ጊዜ በሙሉ ተሳትፎ የእድሉ ተጠቃሚ በመሆን አገራቸውን እና ህዝባቸውን በማንኛዉም መልኩ ለማሳደግ ቆርጠው ተነስተዋል። ሙስሊም ተማሪዎች በትምህርት ተቋማት ውስጥ እያጋጠሟቸው ላሉ ችግሮች እጅ ሳይሰጡ አገራቸው እና ህዝባቸው ለሚጠብቅባቸው ሃላፊነት እራሳቸውን እያዘጋጁ ይገኛሉ።

ሆኖም ግን በቅርቡ በትምህርት ሚኒስቴር ረቅቆ ለውይይት የወጣውና ሃይማኖታዊ ስርዓትን እንዲዳኝ የታሰበው የትምህርት ተቋማት ደንብ በተለይ ሙስሊሙን ህብረተሰብ በእጅጉ አሳስቦት ይገኛል። በድር የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ፌደሬሽንም ከአጋር ሙስሊም ማህበራት ጋር በመተባበር ይህን አገራችን የጀመረችዉን መልካም ራዕይና ብሩህ ተስፋ የሚያኮላሽ መመሪያ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ፣ ልዩ ኮሚቴም አቋቁሞ ጉዳዩን ካጠና እና በቅርበትም ከተከታተለ፤ ሰፊዉን የሙስሊም ህብረተሰብም በጉዳዩ ላይ ካወያየ በኋላ ይህን የአቋም መግለጫ አውጥቷል።

## <u>ከረቂቅ መመሪያው ያገኘነው መልዕክት</u>

የፌደራል ድሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መንግስት የትምህርት እና ስልጠና ፓሊሲ በፊት የነበረው የትምህርት አላማዎች "የህብረተሰቡን ፍላጎት ከግምት ያላስገቡ እና የወደፊት አቅጣጫንም የማያመላከቱ" (ገጽ 2) መሆናቸውን በመግለጽ ትምህርት ለአንድ አገር አጠቃላይ እድገት መሰረት በመሆኑ "የመንግስት ልዩ ትኩረት የሚቸረው እና ቅድሚያም የሚሰጠው" መሆኑን ያመላከታል (ገጽ 4)። ከትምህርት እና ስልጠና ፓሊሲ አጠቃላይ አላማዎቹ መካከልም:-

> "*የሰው ልጆችን መብት የሚያከብሩ፣ ለህዝብ ደህንነት፣ ለእኩልነት፣ ለፍትህና ሰላም ቋሚ የሆኑ፣ በዲሞክራሲያዊ ባህል እና ስነ-ምግባርም የተካኑ ዜጎችን ለማፍራት*" (2.1.4)

የሚለው ሲገኝ ከዝርዝር አላማዎቹ ዉስጥም ተመሳሳይነት ያላቸው ነጥቦች ሰፍረው እናገኛለን።

> "*ዲሞክራሲያዊ ባህልን፣ መቻቻልን እና ልዩነትን በሰላም የመፍታት አቅምን የሚያዳብር እንደዚሁም ለህብረተሰቡ ያለበትን ሃላፊነትን የመወጣት ስሜትን ለማሳደግ የሚያስችል ትምህርትን ለመስጠ (2.2.9)*

> "*ለዲሞክራሲያዊ አንድነት፣ ነጻነት፣ እኩልነት፣ ልዕልና እና ፍትህ እንደዚሁም በመልካም ስነ-መግባር የተካነ ዜጋ ለማፍራት የሚያስችል ትምህርት ለመስጠት*" (2.2.10)

እንግዲህ በትምህርት ሚኒስቴር ረቅቆ የቀረበውን ደንብ ስናጠና፣ የያዘውን መልዕክትም ለመረዳት ጥረት ስናደርግና እዉን ለማድረግ ያሰበውን አላማ ስናገናዝብ ረቂቁ አስፈላጊነቱን ለመግለፅ ከጠቀሳቸው የህገ መንግስቱ አንቀጾች (አንቀፅ 25፣ 27 እና 90(2)) እና በትምህርት እና ስልጠና ፓሊሲው ውስጥ በነጥብ 2.2.7 "ሴኩላር የሆነ ትምህርት ለመስጠት" ከሚሉት በተጨማሪነት ከላይ የጠቀስናቸውን ከግምትም አስገብተናል። በዚህም መሰረት ረቂቁ:-

1. የተለያዩ የትምህርት ተቋማት ያላቸውን ልዩ ባህሪ እና ይዘት ከግምት ሳያስገባ ከመዋለ ህጻናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና በተቋማቱ ሰራተኞች ዘንድ ጭምር በተመሳሳይ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን የታሰበ፤

2. በዜጎች መካከል ልዩነት ላለማድረግ (ህገ መንግስቱ አንቀፅ 25) እና "ሴኩላር የሆነ ትምህርት ለመስጠት" (የትምህርትና ስልጠና ፓሊሲ ነጥብ 2.2.7) በሚል ሽፋን የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ለሀገሪቱ ዜጎች ያረጋገጠውንና እጅግ መሰረታዊ የሆነውን የዜጎችን የሃይማኖት ነጻነት (አንቀፅ 27) የሚከድ፤

3. እንደመሠረት ያስቀመጣቸውን የህገ መንግስቱን አንቀጾች (አንቀፅ 25፣ 27፣ 90(2)) እና ከትምህርትና ስልጠና ፓሊሲ የጠቀሰዉን ነጥብ (ነጥብ 2.2.7) አጣሞ የተረጎመ፤

4. ለማሳካት ያለመው ዓላማ በተለይ በቁጥር 5.3 የተቀመጠው (*በህገ መንግስቱ የተረጋገጡ የሃይማኖት እኩልነት እና ነፃነትን በትምህርት ተቋማትም ተግባራዊ ለማድረግ)* በዉስጡ ካዘለው መልዕክት ጋር በፍፁም የማይጣጣም፤

5. ስለ ሴኩላራዊ አስተዳደር እና ሴኩላራዊ የትምህርት አሰጣጥ የተሳሳተ ግንዛቤን የያዘ፤ በአገሪቱ እውን ሆኖ ያለውን የሴኩላሪዝም አተረጓገምም ሆነ አለም ላይ ካሉ አገሮች እና ታዋቂ የትምህርት ተቋማት ተሞክሮን ለመከተል ያልፈለገ፤

6. በዝርዝር ባስቀመጣቸው አበይት ጉዳዮች ላይ ማለትም የአለባበስ፣ የአምልኮ እና የአመጋገብ እንደዚሁም ትምህርት የሚሰጥበትን የጊዜ ሰሌዳ በተመለከተም የሙስሊሙን ህብረተሰብ የሀይማኖታዊ ግደታ እና ልዩ የጸሎት ባህሪ ከግምት ያላስገባ፤

7. ረቂቁ ሙስሊም ባልሆኑ ኢትዮጵያዊያን እምነት ላይ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በተመለከተ አስተያየት ለመስጠት ባይዳዳንም በአጠቃላይ ይዘቱ እና አላማው የሙስሊሙን ተማሪ እና አጠቃላይ የሙስሊሙን ህብረተሰብ የሃይማኖት ነጻነት የሚጋፋ፤ ማንነቱን ጥያቄ ውስጥ ያስገባ፤ ሙስሊሙ ህብረተሰብ በአገሩ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ሙሉ ተሳታፊ ለመሆን እያደረገ ያለውን ጥረት የሚያመክን፤

8. በዚህም ሙስሊሙ ከእምነቱ ወይንም ከትምህርቱ እንዲመርጥ የሚያስገድድ፤

9. መንግስት በትምህርት ፓሊሲዉ እውን ለማድረግ ላሰበው አላማ የተማሪዎች የመንፋሳዊ ፍላጎቶች መሟላት ያለውን ድርሻ የካደ፤

10. በአገራችን በተለያዪ እምነቶች መካከል መቻቻል እና የእምነት ልዩነት ሳይገድበው ለመላዉ ኢትዮጵያዊ አሳቢ የሆነ ትውልድን ለማፍራት ከመደበኛ ትምህርት ጎን ለጎን የእምነት ማእከላት የሚኖራቸው አስተዋፆ ያልታየው፤

11. የሰው ልጆችን ፍላጎት ለምግብ፣ ለመጠለያ እና አልባሳት ባሉት ፍላጎቶች ብቻ በመወሰን ዝቅ የሚያደርግ፤ ስብዕናን የሚያጓድል፤

12. አገሪቱ እውን ለማድረግ እየጣረች ባለው የዜጎች የሰብአዊ መብት መከበር፣ የዲሞክራሲያዊ ባህል ማደግ እና የመልካም አስተዳደር መዳበር ላይ እንቅፋት የሚሆን፤

13. ሰላምን አምጭ ሳይሆን ላልተፈለገ ፍጥጫ እና ግጭት የሚዳርግ፤ ጥላቻን የሚያዳብር፤ በመንግስት እና በዜጎቹ መካከል አለመተማመንን የሚያጎለብት መመሪያ ሆኖ አግኝተነዋል።

ይህም በመሆኑ ረቂቁን አሁን ባለው መልኩ የማንቀበለው መሆኑን ስንገልጽ የዲያስፖራው ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ልዑካን ቡድን በሚያዚያ 1999 ወር በሙስሊም ተማሪዎች ላይ ያለውን በደል እና አጠቃላይ የሙስሊሙን ችግሮች አንስቶ ከአገሪት ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር በተወያየበት ወቅት የደረሰበትን መግባባት እና መረዳዳት የሚያደፈርስ እርምጃም ሆኖ አግኝተነዋል።

ከላይ ከዘረዘርናቸው ነጥቦች በመነሳትም የሚከተለውን ጥሪ እናቀርባለን፡-

1. የትምህርት ሚንስቴር ይህን ረቂቅ አሁን ባለው መልኩ የመተግበር እርምጃ እንዳይወስድ፤

2. ረቂቁ ያነሳቸው የአለባበስ፣ የአምልኮና የምግብ ጉዳዮችን በተመለከተ የሀይማኖቱን እና የሙስሊሙን ህብረተሰብ ፍላጎትና አቋም አስተዳደራዊ ሥራን ለማከናዎን በተቀመጠ አካል የሚወሰን ሳይሆን የሃይማኖቱ እውቀት ያላቸው ሊቃውንቶችን (ዑለማዎችን) የሚመለከት በመሆኑ አገር አቀፍ የዑለሞች ጉባኤ በአስቸኳይ ተጠርቶ በእነዚህ ሶስት ጉዳዮች ላይ ማሰሪያ እንዲያደርግ፤

3. ቀና አስተሳሰብ ካለ በቀላሉ ሁሉንም ህብረተሰብ ክፍል በሚያረካ መልኩ እልባት ሊሰጥበት የሚችል ጉዳይ፤ ነገር ግን ይህ ሳይሆን ከቀረ የአገራችንን የአጭርና የረጅም ጊዜ የእድገት፣

የዲሞክራሲ፣ የሰላምና የመረጋጋት ፋላጎት ስለሚያጨልም መንግስት ትኩረት ሰጥቶ እንዲከታተለው፤

4. ሙስሊሙ ህብረተሰብም የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት እንዲወያይበት እና ፍላጎቱን ሰላማዊ እና አግባብ ባለው መልኩ ግልፅ እንዲያደርግ፤

5. በተለይም የሙስሊሙን ጉዳይ እንከታተላለን ብለው በሀላፊነት የተቀመጡ አካላት ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ፤

6. ሙስሊሙ ተማሪ ከእምነቱ እና ከትምህርቱ የቀረበለት ምርጫ አግባብነት ያለው ባለመሆኑ በምንም መልኩ የመማር መብቱን ሳይጥልና ትምህርቱን ሳያቋርጥ የእምነት ነጻነቱን ለማስከበር አንድነቱን ጠብቆ እንዲታገል፤

7. የኢትዮጵያ የትምህርት ተቋማት ህብረተሰብ በሙሉ የእምነት ልዩነት ሳይለየው ይህን ለአገራችን እና ለህዝባችን አደጋን ያነገበ፣ አገሪቱን እና ህዝቦቿን ሰላም እና መረጋጋትን የሚከድ ደንብ እንዲቃወሙት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

መላው የዲያስፖራ ሙስሊም ህብረተሰብ ለጉዳዩ ፍትሀዊ የሆነ መፍትሄ ለመሻት ከህዝባችን ጎን በመሰለፍ አስፈላጊዉን ሁሉ ጥረት እንደሚያደርግ ጨምረን እንገልጻለን።

በድር የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ፌደሬሽን
በአውሮፓ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ኔትወርክ
በመካከለኛው ምስራቅ፣ በኤሲያና እና በአሽኒያ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ማህበራት

Tuesday, 08 January 2008